



# ከዝቅተኛነት ስሜት እንሽሽ

የሰይጣን የመጨረሻ ዓላማው አማኞችን ታግሎ ከጣለ በኋላ ሙሉ በሙሉ በቁጥጥሩ ሥር ማድረግ ነው። ለዚህ ነው የክርስትና ሕይወት ሁልጊዜ የትግል ሕይወት የሆነው። ትግሉም ረጅም እንጂ ዛሬ ተጀምሮ ነገ የሚያልቅ አይደለም። አማኝ ከሰይጣንም ጋር በሚያደርገው ትግል ሁልጊዜ ማሸነፍ ብቻ ሳይሆን የሚያደናቅፍበትም ጊዜ ይኖራል። ሰይጣን በማያዳግም ሁኔታ ክርስትያኖችን ታግሎ ለመጣል ልዩ ልዩ ዓይነት ዘዴዎችን ይጠቀማል። ከእኛ በፊት መጥተው ያለፉትን መንፈሳዊ አባቶቻችንን የሕይወት ታሪክ ስንመረምር፥ በህይወታቸው ሁልጊዜ ሳይሸነፉና ሳይደክሙ፥ ቀጥ ብለው የሄዱ ያቀዱትና የወሰኑት ሳይዛባ ሁሉ ነገር ልክ የመጣላቸው እንዳልነበሩ ተረድተናል። በሕይወታቸው አሸናፊ ነበሩ ብለን የምንላቸውን ታላላቅ መንፈሳውያን አባቶች በተለያየ ጊዜ ብዙ ዓይነት የመሸነፍ ጽዋ ጠጥተው ያለፉ ናቸው።

ሰይጣን ከሚጠቀምባቸው ዘዴዎች አንደኛውና ትልቁ ሰው በራሱ ተስፋ እንዲቆርጥ ማድረግ ነው። አማኝ በተደጋጋሚ መውደቅና መነሳት ሲበዛበት “እኔ ክርስትያን መሆን አልችልም፤ እኔ ጌታን ማገልገል አልችልም፤ እኔ ፍጹም የማልረባ ሰው ነኝ፤ ብጀምረውም ተመልሼ መውደቄ አይቀርም” በማለት ተስፋ በመቁረጥ ትግሉን ያቆማል። በዚህም ሰይጣን ደስ ይለዋል። በዓለም ላይ መጥተው ያለፉ በሕይወታቸው ትላልቅ ነገር የሠሩ ለዓለም ዕድገትና ብልጽግና ትልቅ አስተዋጾ ያደርጉ ሰዎች ቀደም ሲል በደረሰባቸው መሸነፍ ወይንም ሰዎች ስለ እነርሱ የሰጡትን መጥፎ አስተያየት “ልክ ነው” ብለው በመቀበል “እኔ እውነትም ሰዎች እንደሚሉት አልረባም፤ ደደብ ነኝ” ብለው ቢሉ ኖሮ ዛሬ ዓለም በትልቅነታቸው አያስታውሳቸውም ነበር። ደካማነታቸውን በወቅቱ ቢረዱም፥ የዝቅተኛነት ስሜት ወደ ኋላ ሳይጎትታቸው ደጋግመው በመሞከራቸው የተነሳ አሸናፊዎች መሆን እንደቻሉ ታሪክ ይመሰክራል።

የታወቀው ሳይቲስት የነበረው አይንስታይን (Einstein) አራት ዓመት እስኪ ሆነው ድረስ መናገር እንዲሁም 7 ዓመት እስኪሞላው ድረስ ማንበብና መጻፍ አይችልም ነበር። የመጀመሪያውን የአንስታይንን ሁኔታ ተምልክቶ “አንስታይን ደካማ ነው፤ ወደ ፊትም ምንም ተስፋ የለውም” ያለ ሰው ቢኖሮ፥ የአንስታይንን መጨረሻ ሲያይ ግምቱ ልክ እንዳልነበረ መረዳት የሚያስቸግረው አይመስለንም።

ዝነኛው የሙዚቃ ደራሲ ቤትሆቨን (Beethoven) የሙዚቃ አስታማሪው አንድ ጊዜ “ቤትሆቨን የሙዚቃ ደራሲ ለመሆን ፈጽሞ ተስፋ የለውም” አለች። ያች የቤትሆቨን አስተማሪ፥ የቤትሆቨንን መጨረሻ ስታይ ምን ያህል እፍረት ተሰምቷት ይሆን? ቶማስ ኤድሰን፥ ልጅ በነበረበት ዘመን አስተማሪው “ቶማስ ኤድሰን ምንም የማይረባ፣ ደደብ ልጅ ነው” ብሎ አስተያየት ሰጠ። ቶማስ ኤድሰን እንደ ተባለው አልሆነም። የኤሌክትሪክ አምፖልን ለመጀመሪያ ጊዜ የፈለሰፈ ዓለም ያደነቀው ሳይንቲስት ሆነ። ቶማስ ኤድሰን በአስተማሪው አስተያየት ተደናቅፎ ተስፋ ቢቆርጥ ኖሮ በዓለም ተደናቂ ሰው ባልሆነም ነበር። የታወቀው አሜሪካዊ ሀብታም ኤፍ ደብልዩ ውልወርዝ (F.W. Woolworth) የሃያ አንድ ዓመት ወጣት በነበረበት ጊዜ አንድ ሱቅ ውስጥ ተቀጥሮ ይሠራ ነበር። ምንም ዓይነት የንግድ ችሎታ የሌለው ሰው ነው ብለው ቀጣሪዎቹ ስለገመቱ፥ ገበያተኞችን እንዲያስተናግድ አልተፈቀደለትም ነበር። ይሁን እንጂ ውልወርዝ እንደተባለው ሳይሆን፥ በንግድ ከፍተኛ ችሎታ ያለው ሰው በመሆኑ፥ በአሜሪካ ውስጥ የታወቀ ሃብታም ነጋዴ ሆነ።

ዋልት ዲዝኒ (Walt Disney) የተባለው ሰው አሜሪካ ውስጥ ለምንኖር ስሙ እንግዳ አይደለም። ባለ ብዙ ሚሊዮን ብር ባለጠጋ የዲዝኒ ወርልድ መሥራች ሰው ነው። አንድ ጊዜ ለአንድ ጋዜጣ አሳታሚ ድርጅት ተቀጥሮ በሚሠራበት ወቅት፥ “ችሎታ የለውም” ተብሎ የተባረረ ሰው ነበር። መጨረሻው ግን እንደ ተባለው ችሎታ የሌለው ሰው ሳይሆን፥ ዓለም ያወቀውና ያደነቀው ሰው ሆኖ ተገኘ።

ድምጻዊ ሙዚቀኛው ካሩስ (Carouse) የሙዚቃ አስተማሪው አንድ ጊዜ "ጥሩ ድምጽ ስለሌለህ፥ ድምጻዊ ተጫዋች መሆን አትችልም" አለችው። ካሩስ ግን በአስተማሪው አነጋገር ተስፋ ባለመቁረጡ፥ ችሎታውን በሥራ አስመሰከረ። አብርሃም ሊንከን፥ የታወቀው አሜሪካዊ ፕሬዚዳንት፥ በሕይወቱ በብዙ ትግልና ፈተና ውስጥ ያለፈ ሰው ነበር። ይሁን እንጂ ተስፋ አልቆረጠም። የሃያ ስድስት ዓመት ወጣት በነበረበት ጊዜ በጣም የሚወዳት እጮኛው ድንገት ሞተችበት። በዚህም ምክንያት ትልቅ የአዕምሮ ስብራት ደረሰበት። በሃያ አምስት ዓመት ውስጥ ልዩ ልዩ የፖለቲካ ውድድር ውስጥ ገብቶ ከአሥሩ በስምንቱ ተሸንፎአል። አብርሃም ሊንከን የደረሰበትን ዓይነት ተደጋጋሚ መሸነፍ ሌሎች ሰዎች ደርሶባቸው ቢሆን ኖሮ፥ ቶሎ ተስፋ ቆርጠው ትግላቸውን ባቋረጡ ነበር። አብርሃም ሊንከን ግን ተስፋ ባለመቁረጡ በመጨረሻ የአሜሪካ አሥራ ስድስተኛው ፕሬዚደንት መሆን ቻለ።

ብዙዎቻችን በሕይወታችን አንድ ጊዜ መሸነፍ ቢደርስብን፥ ወይንም ስለ እኛ ቀና አስተያየት የሌላቸው አንዳንድ ሰዎች መጥፎ የሆነ አስተያየት ቢሰጡ፥ ያንን አምነን በመቀበል የዝቅተኛነት ስሜት (Inferiority complex) እንዲሰማን ሆነን ቶሎ ተስፋ ቆርጠን ትግላችንን እናቋርጣለን። "የዝቅተኛነት ስሜት" ትህትና ማለት አይደለም። የታወቀው እንግሊዛዊ ሰባኪ የነበረው ስፐርጀን "ትህትና ማለት ሰው ስለ ራሱ ትክክለኛ ግምት ሲኖረው ነው፤ ይኸውም ከሆነው በላይ እራሱን አተልቆ እንዳያይ፥ ወይንም ከሆነው በታች እራሱን ዝቅ አድርጎ እንዳይመለከት ነው" አለ። ትራየን ኤድዋርድ የተባለው ሰው ተመሳሳይ አስተያየት ሲሰጥ እንሰማለን። "እውነተኛ ትህትና እራስን እንደ ጉድፍ እንደ ጥራጊና እንደምናምንቴ አድርጎ መናቅ ሳይሆን፥ እግዚአብሔር እንደሚያየን ትክክለኛ የሆነ ግምትና አስተያየት ስለ እራሳችን ሲኖረን ማለት ነው" አለ።

### ሰው በተፈጥሮው ትልቅ ነው

ሰው በሰውነቱ ወይንም በአካሉ ውስጥ የኒው ዮርክን ከተማ ለማጥፋት የሚያስችል የአቶሚክ ቦምብ ንጥረ ነገር እንዳለው ሳይንቲስቶች ይናገራሉ። የሰው የማሰብ ችሎታ ምን ያህል ትልቅና ወሰኑ የሰፋ መሆኑን በቁጥር ይህን ያህላል ብሎ ማስቀመጥ በጣም ያስቸግራል። የሰው አዕምሮ ወይንም ጭንቅላት ሊሠራ የሚችለውን ነገር በኤሌክትሮኒክስ ኮምፒዩተር መሥራት ቢሞከር ያ ኮምፒዩተር ትልቅነቱ ሃያ ሁለት ፎቅ ያለው የትልቅ ህንጻ መጠን ይኖረው እንደ ነበር ሳይንቲስቶች ይናገራሉ። የሰው አዕምሮና አካል ሊሠራው የሚችለው አስደናቂ ነገር ይህን ያክላል ብሎ መገመት እጅግ በጣም ያስቸግራል። መጽሀፍ ቅዱስም የሰውን ታላቅነት ይናገራል። "አንተ እርሱን ታስበው ዘንድ ሰው ምንድነው? እርሱንስ ትጎበኘው ዘንድ የሰው ልጅ ምንድነው? ከመላዕክት በጥቂቱ ብታሳንሰውም የክብርና የምስጋና ዘውድ ጫንህለት፤ በፈጠርሃቸው ፍጥረቶች ሁሉ ገዢ አድርገህ ሾምኸው፤ ከፍጥረትም ሁሉ በላይ አደረግኸው" ይላል (መዝ. 8፥4-6)። ይሁን እንጂ አንዳንድ ሰዎች የእግዚአብሔር አስደናቂ የእጆቹ ሥራዎች መሆናቸውን ይዘነጉና እራሳቸውን እንደ ጉድፍ ሲቆጥሩ ይታያሉ። ያ ብቻ ሳይሆን መኖር ሰልችቶአቸው፥ የራሳቸውን ሕይወት በገዛ እጃቸው ያጠፋሉ። "ማሆል" የተባለ ጸሀፊ "ትዕቢተኛ ሰው እግዚአብሔር የለውም፤ ምቀኛ ሰው ጎረቤቱ ይሸሸዋል፤ ከራሱ ጋር የሚጣላ ሰው እራሱን ያጣ ነው፤ ታዲያ ያ ሰው፥ እግዚአብሔር ከሌለው፣ ጎረቤት ካጣ፣ ከራሱ ጋር ከተጣላ፣ ምን የጨበጠው በጎ ነገር አለው?" ሲል ተናገረ። የዝቅተኛነት መንፈስ የሚያጠቃቸው ሰዎች በአዕምሮአቸው ደካሞችና ዝቅተኞች ስለሆኑ አይደለም። እንዲያውም የሚገርመው ነገር፥ ጥሩ አዕምሮ ያላቸው ሰዎች ከሌሎች ይልቅ ብዙ ጊዜ የዝቅተኛነት መንፈስ ሲያጠቃቸው ይታያሉ። የዝቅተኛነት መንፈስ የሚሰማቸው ሰዎች አቋማቸውን በግልጽ ለሌሎች ያሳያሉ ማለት አይደለም። በተቻለ መጠን ተደብቆ በውስጣቸው እንዲቀር ይሞክራሉ። አንዳንዶችን የዝቅተኝነት ስሜታቸውን ለመደበቅ የሚጠቀሙበት ዘዴ በግልጽ ያስታውቃል።

### የዝቅተኛነት ስሜት ባህሪ

1. አንዳንድ የዝቅተኛነት ስሜት የሚያጠቃቸው ሰዎች፥ ስሜታቸውን ለመደበቅ የሌላቸውን ትልቅነት እንዳላቸው አድርገው ለማሳየት ይታያሉ። ላቫተር የተባለ ጸሐፊ "ብዙ ማስመሰል ካለበት፥ ያ ነገር በብድር ወይም በውሰት የመጣ ነው። ሁልጊዜ ተፈጥሮአዊ የሆነ ነገር ሁሉ ማስመሰል የለበትም" ይላል። እራሳቸውንና ቤተሰባቸውን ችግር ውስጥ ከተውም ቢሆን፥ ከአቅማቸው በላይ የሆነ ውድ ልብስ በመልበስ፥ እቤታቸው ውስጥ ውድ ዕቃ ገዝተው በመደርደር የዝቅተኛነት ስሜታቸውን ለመደበቅና ትልቅነታቸውን ለሌሎች ለማሳየት ሲሞክሩ ይታያሉ።
2. የዝቅተኛነት ስሜት የሚያጠቃቸው አንዳንድ ሰዎች ብዙ ጊዜ ስለ ማንኛውም ሰው ቀጥተኛ አስተያየት መስጠት አይሆንላቸውም። አሽሙረኞች ወይንም አሽሟጣጮች ሆነው ይታያሉ። የሌላውን ሰው ስም ወይንም ዝና ሲያፈርሱ እንጂ ሲገነቡ አይታዩም። ሌላውን አሳንሰው በመናገራቸው የራሳቸውን ትልቅነት ማሳየት የሚችሉ መስሎ ይታያቸዋል።
3. የዝቅተኛነት ስሜት የሚሰማቸው ሰዎች በቀላሉ ይበረግጋሉ። ከእነርሱ የተሻለ መስሎ ከሚታያቸው ሰው

አካባቢ ይሸሻሉ፤ ወይንም ያ ሰው በአካባቢያቸው እንዲገኝ አይፈልጉም። ብዙ ጊዜ እራሳቸውን ከሰው ያሸሻሉ። ብቸኝነታቸውን ይወዱታል።

4. የዝቅተኛነት ስሜት የሚሰማቸው ሰዎች፥ ማንኛውም ቀጥተኛና ትክክለኝ ንግግር እነርሱ ጆሮ ሲደርስ የሚገባቸው ልዩ ትርጉም ይዞ ነው። ነገር ይተርጉማሉ። “እንዲህ ማለቱ እኔን ሊነካኝ አይደለም?” በማለት አስተያየት ሲሰጡ ይሰማሉ። ሁለት ሰዎች ጎን ለጎን ቀስ ብለው ሲያወሩ ቢያዩ “እኔን እያሙኝ ነው፤ ስለ እኔ መጥፎ ነገር እይተነጋገሩ ነው” የሚል ፍርሃት ይሰማቸዋል። ሁልጊዜ ተጠራጣሪዎች ናቸው። የዝቅተኛነት መንፈስ በቀላሉ የሚታይ ነገር አይደለም። ቻርለስ ስዊንደል “የዝቅተኛነት መንፈስ በሰው ልብ ሥር የተደበቀ “ሰው በላ” አውሬ ነው” ይለዋል። ብዙዎች እራሳቸውን በገዛ እጃቸው ከሚያጠፉት ሰዎች መካከል አብዛኛዎቹ የዝቅተኛነት መንፈስ የሚያጠቃቸው ናቸው።

### ሀ) ሙሴ ዝቅተኛነት ተሰምቶታል

ሙሴን የሚያክል ታላቅ የእግዚአብሔር ሰው “የዝቅተኛነት መንፈስ” ያጠቃዋል ብሎ መገመት ያስቸግራል። ይሁን እንጂ በዚህ ስሜት አልፎአል። ይህን ዓይነት ስሜት ቢሰማውም አይገርመንም። ምክንያቱም በሕይወቱ ውስጥ አንዳንድ ጤናማ ያልሆነ ነገር ስለ ደረሰበት ነው። ሙሴ የበደለኛነት ስሜት እንደነበረበት እንገምታለን። የበደለኛነት ስሜት ብዙ ጊዜ የዝቅተኛነትን ስሜት ያስከትላል። ሙሴ በግብጽ በነበረበት ዘመን አንድ ግብጻዊ ሰው ገድሎ ወደ ምድያን በረሃ ተሰዶ በበግ ጠባቂነት የሚኖር ተራ ሰው ነበር። አርባ ዓምት ሙሉ በግ ከመጠበቅ በስተቀር “ይህን ሠራሁ” ብሎ የሚለው ነገር አልነበረውም። እንዲያውም ከነጭራሹ በወገኖቹ የተረሳ ሰው ነበር።

በዚህ ስሜት ውስጥ እያለ፥ እግዚአብሔር አንድ ቀን ሙሴን “እነሆ አሁንም ሕዝቤን ከግብጽ ምድር ታወጣ ዘንድ ወደ ግብጽ ንጉሥ እልክሃለሁ” (ዘጸአት 3፥10) አለው። ሙሴ ግን “ወደ ፈርዖን ሄጄ እስራኤልን ከግብጽ ለማውጣት የምበቃ ሰው አይደለሁም” (ዘጸአት 3፥11) ሲል መለሰለት። ሙሴ የታየው ብቃቱ ሳይሆን ድካሙ ነው። እርግጥ ነው ሙሴ በግብጽ አለ የሚባለውን ከፍተኛ ትምህርት ተምሮ ነበር። አስተዳደር ችሎታ እንደሆነ በፈረዖን ቤት በነበረበት ጊዜ በቂ ልምምድ ነበረው። ይሁን እንጂ በራሱ መተማመን አቃተው። ይሄ ሙሴ የተሰማው ስሜት የትህትና ስሜት ሳይሆን የዝቅተኛነት ስሜት ነበር። አርባ ዓመት በከንቱ በግ በመጠበቅ ብቻ ስለ አሳለፈ፥ ብቁነቱ አልታየውም ነበር። እውነተኛ ትሁት ሰው በእግዚአብሔር ላይ ከፍተኛ እምነትና ትምክህት ያለው ሰው ነው። እግዚአብሔር “በሕይወትህ ታላቅ ሥራን እሠራለሁ” ሲለው ሠሪው እግዚአብሔር መሆኑን ስለሚያውቅ አምኖ ይቀበላል።

እግዚአብሔር ሙሴን ወደ “ፈርኦን ሂድ” ሲለው “አልሄድም፤ እኔ ማን ነኝ?” ሲል እግዚአብሔርን ክርክር ገጠመው። ሙሴ የዘነጋው፥ እሥራኤላውያንን ነጻ የሚያወጣው እግዚአብሔር እንጂ እርሱ አለመሆኑን ነው። እርሱ ተራ መሣሪያ እንጂ ነጻ አውጪ አልነበረም። ለዚህ ነው “እኔ ማን ነኝ?” ሲል የጠየቀው። ትክክለኛው መልስ “አዎን! ሙሴ አንተ ነጻ አውጪ አይደለህም” የሚል ነው። እግዚአብሔርም የሙሴን ፍርሃት ለማጥፋት “አይዞህ እኔ ከአንተ ጋር ነኝ” አለው። ይሄም ተስፋ ስለ አላጠገበው “እስራኤላውያን እግዚአብሔር አልተገለጠልህም ብለው ባያምኑኝና ቃሌን ባይሰሙ ምን እላቸዋለሁ አለው” (ዘጸአት 4፥1)። ለዚህም ጥያቄ መልስ እንዲሆንለት በፈሮን ፊት የሚያደርገውን ተአምር አሳየው። ያም ስላልበቃው “እባክህ ጌታ ሆይ! ወደዚያ አትላከኝ፤ ቀድሞም ሆነ ወይም አሁን አንተ ከእኔ ጋር መነጋገር ከጀመርህበት ጊዜ አንሥቶ የመናገር ችሎታ የለኝም፤ እኔ አንደበቴ የሚኮላተፍና አጥርቼ ለመናገር የማልችል ነኝ” (ዘጸአት 4፥10) ሲል መለሰለት። እግዚአብሔርም “እኔም ከአንተ ሆኜ መናገር እንድትችል አደርግሃለሁ፤ ምን መናገር እንደሚገባህ እነግርሃለሁ” (ዘጸአት 4፥12) አለው። ሙሴም ያ ስላላረካው “እባክህ ጌታ ሆይ ሌላ ሰው ላክ” አለው (ዘጸአት 4፥13)። እግዚአብሔርም ሙሴን ተቆጥቶ አሮን እንዲረዳው ሰጠው።

..........................................................................................

**በሚቀጥለው ክፍል እስክንገናኝ፥ የጌታ ጸጋና ሰላም ከሁላችን ጋር ይሁን።**